# አቶ ከድር ዋበላ/ Kedir Wabella



**July 1, 1957 – March 13, 2016**

# የአቶ ከድር ዋበላ አጭር የሕይወት ታሪክ

## “መልካም ምግባር ከመቃብር በላይ ይውላል።”

አቶ ከድር ዋበላ ከአባቱ ከዋበላ ሣሊሃ ከእናቱ ከወሮ ሻይቴ አሻውካ በሐምሌ ፳፫ ቀን ፲፱፻፵፱ ዓም / JULY 1, 1957 በሸዋ ክፍለ ሃገር በናዝሬት ከተማ ተወለደ። አቶ ከድር በአፄ ገላውድዮስ የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን የተከታተለ ሲሆን በእድገት በህብረት ዘመቻ በአሰበ ተፈሪ ከተማ ዘማች ነበር።

አቶ ከድር በወቅቱ በነበረው ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ለዲሞክራሲ መስፈን፣ ለህግ የበላይነት በሀገራችን መረጋገጥ በቀጥታ በንቃት በመሣተፍ በኢ.ህ.አ.ፓ የወጣት ሊግ ኢ.ህ.አ.ወ.ሊ. ሲሳተፍ ቆይቶ ነገሮች እየከረሩ ሲመጡ በገዛ ሀገሩ በመሰደድ በምንጃር ኤጀሬሳ ተጠልሎ ባለበት በ፲፱፻፸፱ ዓም መጨረሻ በአሳዳጆች እጅ ይወድቃል። በወቅቱ በወጣቶች ላይ የደረሰው መከራ ይህ ነው ባይባልም በእሱ ላይ የደረሰው መከራ ግን የተለየ ነበር። በኢትዮጵያ ውስጥ ከደረሱት የስቃይ ዓይነቶች ሞት የሚያስመኝ ስቃይ ከደረሰባቸው ወጣቶች መካከል በዋናነት ከሚጠቀሰሱት አንዱ ነው።

ከድር ዋበላ የድርጅቱንና የጓደኞቹን ሚስጢር ለመጠበቅ በሰው ላይ ይደርሳል ተብሎ የማይገመት ስቃይ ተቋቁሞ ታማኝነቱን በተግባር ያረጋገጠ፤ ቃልኪዳኑን የጠበቀ፤ ለሀገሩና ለህዝቡ የቁርጥ ልጅ በመሆኑ ፍከች ያላለ የያ ትውልድ ጀግና ነው። ከድርን ላየውና ለተመለከተው ሁለቱም የውስጥ እግሮቹ ዱላ ሳይሆን ጅብ ቦጭቆ የለቀቀው ጉድጓድ ይመስል ነበር። ለበርካታ ወራት ወላጆቹ የደረሰበትን ሳያውቁ በሰው በሰው በመከራ አፈላልገው ያለበትን ቦታ ከአወቁ በኋላ ምንጃር ድረስ በመሄድ በከፍተኛ ልመና እናቴ ልታዩኝ መጥታለች ይላል።

ሆኖም ከሰውነት ጎዳና የመጣው አካላቱን እንዳይታይ ገራፊዎች በመፈለጋቸው በጋቢ ጠቅልለው ድንጋይ ላይ በማስቀመጥ ለሚወዳቸው እናቱ ለአምስት ደቂቃ እንዲያዩት ተፈቀደለቸው። ታዲያ ጅብሪል ሁሌ ሲናገር እናቴ ስታዬኝ እንደሰው እናት ሳትስመኝ የስስቷ፣ የናፍቆቷና የስጋቷ ብዛት እንደ ላም ጥጃዋን እንደምትልሰው ላሰችኝ የሚለው አባባሉ ሁሌም አንጀትን የሚበላ አሳዛኝ አነጋገሩ ነበር።

ከድር ከአመታት እሥርና ስቃይ በኋላ ተፈትቶ ወደ ቤተሰቡ ተደባልቆ ኑሮውን ሲጀምር እንደእኩዮቹ መሮጥ እንደልቡ መንቀሳቀስ ባይችልም እየተንፏቀቀም እያነከሰም በመጀመሪያ ኬንያ ከዛም ወደ ሱማሌ በመሄድ የስደት ኑሮውን ተያያዘው። በመጨረሻም የአሜሪካን መንግሥት በሰጠው ዕድል ከበርካታ ጓደኞቹ ጋር ወደ አሜሪካ በመምጣት ከጥቂት ወራት በኋላ የጓደኞቹን ዕገዛ የሚሹ የጤና ችግር ስለነበረበት በ1991 መጨረሻ የዋሽንግተን ሲያትል ነዋሪ የሆነ የጅብሪልን ዋበላ የአካል ጉድለቱን የተመለከተ የአሜሪካን መንግሥት እስከዕለተ ህልፈቱ ሲንከባከበው ቆይቷል።

ከድር ዋበላ ላለፉት 39 ዓመታት አልደርቅና አልከስም ያለውን ቁስሉን እንደተሸከመ ኖሯል። ያይን እማኞች ሲገልጹ ዛሬም ድረስ የእግር ቁስሉ ያመረቅዝና ያዥ እነደነበረ ይናገራሉ። ሆኖም ጅብሪል ዋበላ አካላቱ የተቦዳደሰ እንደልቡ እንደሰው ባይራመድም እንደእኩዮቹ ባይሮጥም ስቃዩ እንቅልፍ ቢነሳውም ስብራቱና ቁስሉ አከላቱን ቢያደከመውም ህሊናው ግን ፍፁም ብርቱና ፅኑ እንደነበረ በርካቶች ይናገራሉ።

ከድር በገዛ ሀገሩና ወገኑ ለሰው ልጆች መብት መከበር፣ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ነጻነት መረጋገጥ በመጠየቁ አካሉ በዱላ ቢፈረካከስም እግሩ ተጫምቶ መራመድ ባይችልም እስከመጨረሻው ድረስ ኢትዮጵያን እንዳለ ለህዝቧ ነፃነትን እንደተመኘ አልፏል።

የከድርን የሥነ ጽሑፍ ችሎታን የእሱን ቆራጥነትን አናስተዳጉልበትም። ከድር በሲያትል ከተማ በተደረገው የኢትዮጵያ የነፃነት ትግል ውስጥ ድርጅቱን ሳይለቅ ህጉን እንዳከበረ በተለይም ደግሞ የህዝብን የማወቅ መብት ስለሚያምን በሲያትል በነበሩ የህብረት ሬዲዮና ቴሌቪዥን ላይ በበጎ ፈቃደኝነት ለረጅም ጊዜ አገልግሏል። ከጊዜ በኋላ አቅሙ እየደከመ የእግሩ ጦስ ወደ አንጀቱ ገብቶ ለጥቂት ጊዚያት በሆስፒታል ሲታከም ቆይቶ በተወለደ በ59 ዓመቱ MARCH 13, 2016 ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቷል።መስዋዕት የሆነላቸው አላማዎቹና ተጋድሎዎቹ ነገ ለምትመሠረተው ኢትዮጵያ መሠረት እንደሚሆንና ትውልድ ሲዘከረው የሚኖር መሆኑን ተስፋ እያደረግን ጅብሪልን ዛሬ እንሰናበተዋልን።

በጠቅላለ በሲያትል ኮሚኒቲ ለወንድማችን እና ለልጃችን ለከድር ዋበላ ላደረጋችሁት ቤተሰቦቹ ምስጋና ያቀርባሉ::

ከድር ዋበላ እንወድሃለን
የከፈልከውን መስዋዕትነት እናከብራለን፣ እንናገራለን
ኢትዮጵያ ነፃ ወጥታ ተጋድሎህን እንመሰክራለን
ሁሌም በልባችን እናስብሃለን




ክርስቲያን እስላሙን በእኩል ተመልክቶ
የሀገር ነፃነት የወገንን ፍትህ ከልብ ተመኝቶ
ከድር ዋጋ ከፍሏል እግሩን አስበልቶ
ለአርባ ዓመታት ቁስሉ ሳይደርቅ
በቁስል በስቃይ በህመም ቢማቅቅ
እንደሰው ሳይጓዝ እንደሰው ሳይቦርቅ
በዓላማው የጸና እምነቱን የማይለቅ

እስላም ክርስቲያኑ ከድርን ይመርቅ
ከድር ዋበላ መንፈስ ጠንካራ
አካሉ ቢጎል መንፈሱ ጠንካራ
ሀገሩን ኢትዮጵያን ሁሌም የሚጠራ
ቀኑ ደረሰና በአምላኩ ተጠራ
ልጅ እንኳን ባይኖረው ስሙን የሚያስጠራ
በከፈለው ዋጋ ዘላለም ይታወስ ይጠራ